# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከኦክቶበር 11-20/2022 የነበረው የአየር

## ሁኔታ ግምገማ እና

## ከኦክቶበር 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

## ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦክቶበር 2022
አዲስ አበባ

# ርዕስ ገፅ


ርዕስ ........ i

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ........ 1

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20 /2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ 2

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20 /2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ........ 3

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20 /2022 ድረስ የነበረው የዝና ብመጠን ........ 4

ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........ 4

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ ........ 5

እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 5

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 5

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ........ 6

እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 6

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 6

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ ........ 7

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 22 እስከ ኖቬምበር 1, 2022 የሚኖረዉ ዝናብ በሚ.ሜ መጠን በሚ.ሜ........ 8

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 22 እስከ ኖቬምበር 1, 2022 የሚኖረዉ ዝቅተኛ አየር ሙቀት መጠን......... 8

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 8

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 9


## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

በኦክቶበር ሁለተኛ አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የተስተዋለ ቢሆንም፤ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው የሆኑት የደቡብ ኦሮሚያና የደቡብ ሶማሌ አካባቢዎች ከነበራቸው የደመና ሽፋን በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ ዝናብ አግኝተዋል፡፡ በተጨማሪም በሰሜን ምዕራብ፣ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል። ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከመዘገቡ ጣቢዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በአቦቦ 30.4፣ በአይራ 33.2፣ በአርጆ 36.4፣ በአይከል32.7፣ በቡርጂ 30.6፣ በቻግኒ 55.6፣ በዶሎመና 68.5፣ በጋምቤላ 34.0፣ በጊኒር 30.0፣ በጂንካ 37.9 በሊሙገነት 38.5፣ በማሻ 40.2 እና 30.6፣ በነጆ 36.0 ፣ በሻምቡ 31.2 እና በወላየታ ሶዶ 50.5 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡ በሌላ በኩል የሰሜን ምሥራቅ፣ የመካከለኛውና የምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ተዘወትሮባቸዋል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የለሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ ከዕለት ወደ ዕለት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ጨምሮ ተስተውሏል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከ25-145 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ ከአማራ የመካከለኛው ጎንደር፤ የአዊና የምዕራብ ጎጃም፤ አብዛኛው የቤንሻንጉል-ጉምዝ፣ የጋምቤላና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ከኦሮሚያ በሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ የኢሉአባቦራ፣ የቡኖ በደሌ፣ የጅማ፣ የጉጂና የባሌ ክልል ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች እንዲሁም ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የባስኬቶ፣ የጎፋ፣ የቡርጂና የደራሼ ዞኖች ከ4-10 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በበአብዛኛው አማራና ትግራይ፤ በአርሲ፣ በሰሜንና ምስራቅ ሸዋ፣ በጉጂና ቦረና ዞኖች፣ በኤሊዳር ጣቢያ እንዲሁም በሶማሊ ሁሉም ዞኖች ላይ ከ5-25 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ2-4 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ከርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከአማራ የምዕራብና መካከለኛው ጎንደር የአዊ፣ የምዕራብና ምስራቅ ጎጃም እና የደቡብ ወሎ ዞኖች፤ የቤንሻንጉል-ጉምዝና የጋምቤላ ሁሉም ዞኖች፤ የሲዳማ፤ በሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ የኢሉ አባቦራ፣ የጅማ፣ የአርሲና ምዕራብ አርሲ፣ የባሌ፣ የቡኖ በደሌ፣  የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵየ ክልል ሁሉም ዞኖች፣ የሲዳማ፣ የባስኬቶ፣ የጎፋ፣ የቡርጂና የደራሼ ዞኖች ላይ እንዲሁም የኤሊዳር ጣቢያ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛው ያነሰ የዝናብ መጠን ነበራቸው (ካርታ 3)፡፡


ካርታ 1   ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20 /2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20 /2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20 /2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





ከመደበኛ በታች መደበኛ ከመደበኛ በላይ

# እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የኦክቶበር የሁለተኛ አስር ቀናት የሰሜን ምሥራቅ፣ የመካከለኛውና የምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የተስተዋለ ሲሆንና፤ ይህም ሁኔታ ለደረሱና በመድረቅ ሂደት ውስጥ ለሚገኙ ሰብሎች አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በሌላ መልኩ በሰሜን ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብና በደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ ጥሩ የእርጥበት ሁኔታ የተስተዋለባቸው በመሆኑ፤ የተገኘዉ እርጥበት ቀደም ብለው ለተዘሩና እድገታቸውን ላልጨረሱ፣ አልፎ አልፎ ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙ፤ ዘግይተው ለተዘሩና በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት ከማሟላት አንፃር ገንቢ ሚና ነበረው፡፡ በተጨማሪም በደቡብ የሀገሪቱ ደጋማ ክፍሎች ላይ ዘር ለመዝራትና እንዲሁም በቆላማው አካባቢ ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጥሩ አስተዋፆ የነበረዉ ሲሆን፤ በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው የሆኑት የደቡብ ኦሮሚያና የደቡብ ሶማሌ አካባቢዎች በአንዳንድ ሥፍራዎቻቸው እርጥበት እንደነበራቸው የተሰበሰቡ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 4)።


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ከኦክቶብር 11-20/2022 የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ እንደነበራቸው የተሰበሰቡ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህንን ሁኔታ ተከትሎ በአብዛኛዉ ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ፣ ባሮ አኮቦ፣ አባይ፣ ገናሌዳዋ በጥቂት የላይኛው ተከዜ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ዋቤሸበሌ እንዲሁም የመካከለኛው ስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ላይ ከከፍተኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ አግኝተዋል፡፡ በተጨማሪም የመካከለኛው ተከዜ እና ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት የተስተዋለባቸው ተፋሰሶች ናቸው፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅና ከፊል ደረቅ ሁኔታ አመዝኖባቸው ተስተውሏል (ካርታ 5)፡፡


ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በሚቀጥሉት አሥራ አንድ ቀናት ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በደቡብ ምዕራብና በደቡብ የሀገሪቱ አጋማሽ ክፍሎች ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ የሚቀጥል ሲሆን፤ከዚሁ ጋር ተያይዞ የተለያየ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር ይጠበቃል። በተጨማሪም አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በጥቂት የደቡባዊው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ሊኖር እንደሚችል ይጠበቃል (ካርታ 6)፡፡ ይሁን እንጂ የሰሜን፣ የሰሜን ምስራቅና የመካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የበጋው ደረቃማ፣ ጸሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ ሊቆይባቸው እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የለሊትና ማለዳው ቅዝቃዜ በአንፃሩ ደጋማ ሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከ 5 ዲግሪ ሴልሺየስ በታች ሊሆን እንደሚችል ይጠበቃል (ካርታ 7)፡፡

በዚህም መሰረት ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምዕራብ እና ምሥራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉደሩ፣ ቡኖ በደሌ፣ አርሲና ባሌ፣ የቦረናና የጉጂ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የመካከለኛውና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ምዕራብ ጎጃም እና አገው አዊ ዞን፤ ጥቂት የጋምቤላና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ዞኖች፣ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የወላይታ፣ የዳውሮ፣ የጋሞና ጎፋ ዞኖቸ፣ የከፋና የቤንች ማጂ፣ የደቡብ ኦሞ፣ የጌዲዮ እና የሰገን ህዝቦች እንዲሁም የሲዳማ ዞኖች በአብዛኛው ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ከሶማሌ ክልል ደጋሀቡር፣ ፊቅ፣ ቀብሪደሃር፣ አፍዴር፤ሸበል፣ ሊበን እና ጎዴ መደበኛ የሆነ ዝናብ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በጥቂት ሥፍራዎቻቸው ላይ ከባድ ዝናብ ሊኖር ይችላል፡፡ ከዚህም ሌላ በጥቂት የምዕራብና የምስራቅ ሐረርጌ፣ ዞኖችና፤ ከሶማሌ ክልል በጥቂት የፋፈን ዞኖች፤አብዛኛው የጋምቤላ ክልል ስፍራዎች፤ ከቤኒሻንጉሌ ጉሙዝ የካማሽና መተከለ ዞኖች በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ አነስተኛ ዝናብ ይኖራል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች ደረቅ ሆነው ይቆያሉ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 22 እስከ ኖቬምበር 1, 2022 የሚኖረዉ ዝናብ በሚ.ሜ መጠን በሚ.ሜ.

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 22 እስከ ኖቬምበር 1, 2022 የሚኖረዉ ዝቅተኛ አየር ሙቀት መጠን በዲግሪ ሴልሺየስ

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የኦክቶበር ሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት የእርጥበት ሁኔታው በደቡብ ምዕራብና በደቡባዊው የሀገሪቱ አጋማሽ ክፍሎች ላይ እንዲሁም የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ እንደሚቀጥል የተተነቱኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚገኘዉ እርጥበት በተለያየ ምክንያት ዘግይተው ለተዘሩና የእድገት ጊዜያቸውን ላልጨረሱ የመኸር ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ አቅርቦት ፍላጎታቸውን ለማሟላት እንዲሁም ለአርብቶ አደሩና ለከፊል አርብቶ አደሩ አከባቢዎች ለመጠጥ ውሃ ቅርቦት መሟላትና ለአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ መሻሻል ምቹ ሁኔታን ይፈጠርላቸዋል፡፡ እንዲሁም ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት ጥምር ግብርና ለሚያካሂዱ ለደቡባዊው የሀገሪቱ ክፍሎች አዲስ ለተዘሩም ሆነ በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች የተሟላ እድገት እንዲኖራቸው የሚያስፈልጋቸው የውኃ አቅርቦት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር የሚጠበቅ ሲሆን፤ የእርጥበት ሁኔታው በደቡብና በደቡብ ምስራቅ ለሚገኙ አርብቶ አደርና ለከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የውኃ አቅርቦት ከማረጋገጥ አንፃር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ውኃ አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውኃ ለመሰብሰብና ለማከማችት መልካም አጋጣሚ ስለሚያገኙ ይህንኑ ለማከናወን የሚያስችል ዝግጅት እንዲያደርጉ ይመከራሉ፡፡ በሌላ በኩል በሰሜን፣ በሰሜን ምስራቅና በመካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚያመዝን ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የእድገት ጊዜያቸውን እየጨረሱ ላሉና ተጨማሪ የውሃ አቅርቦት ለማይፈልጉ ሰብሎች እንዲሁም የእድገት ጊዜያቸውን ጨርሰው ለመሰብሰብ ዝግጁ የሆኑ ሰብሎችን ለመሰብሰብ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ሲሆን፤

ከደረቃማው ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ጠንካራ ሊሆንና የውርጭ ክስተትም በአንዳንድ ደጋማ አካባቢዎች የመከሰት ዕድል ይኖራል፡፡ ይህም ሁኔታ በተለይም በአበባና ፍሬ በመሙላት ላይ ያሉ ሰብሎችን ሊጎዳ ስለሚችል አርሶ አደሮች አስፈላጊውን ጥንቃቄ ለማድረግ እንዲችሉ የግብርና ባለሙያዎች ቅርብ ክትትልና አስፈላጊውን እገዛ እንዲያደርጉ ከወዲሁ ይመከራል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21-31/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥራ አንድ ቀናት በአብዛኛው በደቡብ፣ በደቡብ ምስራቅ እንዲሁም በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍል በሚገኙት ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት ሁኔታ ሊኖራቸው እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ያመለክታል፡፡ ይህንን ሁኔታ ተከትሎ በአብዛኛው ባሮአኮቦ፣ ዋቢሸበሌ፣ ገናሌዳዋ፣ ኦጋዴን፣ የመካከለኛው እና የታችኛው ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ እንዲሁም አባይ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በተጨማሪም በጥቂት የላይኛው ገናሌዳዋ፣ ዋቢሸበሌ፣ የላይኛውና የመካከለኛው በሮአኮቦ እና የመካከለኛው አባይ ተፋሰሶች ላይ አነስተኛ እርጥበት መጠን እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፍል ደረቅ ሆነው ይቆያሉ፡፡ በተጨማሪም የበጋ ወር ከመሆኑ ተያይዞ የተገኘውን እርጥበት ከብክነት እና ከብክለት ጠብቆ በአግባቡ መጠቀም እንዲቻል እንመክራለን፡፡